# ግራ የተጋባው የፖሊሲ ሰነድ "ትንተና"

ቶሎሣ ኡርጌሣ Utolosa@yahoo.com

በተግባር ተፈትሾ ያስገኘው ውጤት ብዙ ተብሎለታል፡፡ ትናንት ላይ ሆኖ ዛሬን የሚተልም በመሆኑም፤ በአሁኑ ወቅት ሀገራችን በተለያዩ መድረኮች ላይ ስሟ ከፍ ብሎ እንዲጠራ አድርጓታል፡፡ መሪዎቿም አፍሪካንና ዓለምን በሚወክሉ ታላላቅ ጉባዔዎች ላይ እንዲገኙ፣ ተሞክሮአቸውንም ለሌሎች እንዲያስተላልፉ በማድረግ ረገድ ቁልፍ ሚናን አበርክቷል-በ1995 ዓ.ም በሰነድነት የወጣው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ፡፡

ፖሊሲው ባለፉት 21 የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ዓመታት ለተገኘው አጠቃላይ ውጤት የበኩሉን ድርሻ ማበርከቱ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ በሰነዱ ታግዘው ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በዓለም፣ በአህጉር አቀፍ ብሎም በክፍለ አህጉር ደረጃ የተከናወኑት ወሳኝ የዲፕሎማሲ ድሎች ሀገራችን ከራሷ አልፋ የአፍሪካ ጥቅም አስከባሪ ሆና እንድትመረጥ አስችለዋታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ቡድን-8 እና 20 እየተባሉ በሚጠሩት የዓለምን ኃያላን ሀገራት በሚያደርጉት ስብሰባዎች ላይ ሀገራችን ከጥቂት የአፍሪካ ሀገሮች ጋር እንድትጋበዝና ተሰሚነቷም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ ማድረጉ ሁላችንም በተጨባጭ በማየት ላይ የምንገኘው ዕውነታ ነው፡፡

ይሁንና ይህን የፖሊሲውን ውጤት ማየት የማይሹ፣ ቢያዩም ዓይናቸውን በመሃረብ ለመሸፈን ወደኋላ የማይሉ እንዲሁም በራሳቸው የጥላቻ ዓለም ውስጥ የሚዳክሩ ጥቂት "የሃሜት ፖለቲካ" አራማጆች ሁኔታውን ሊቀበሉት አይፈልጉም፡፡ ከዚህ አኳያ በፍትሕ ጋዜጣ ግንቦት 17/2004 ዓ.ም "ፖለቲካና ሥልጣን" በሚል ዓምድ ሥር የጋዜጣው የጥላቻ ታምቡር ደላቂ ከሆኑት አንዱና "በአዘጋጅነት" ስማቸው የተሰደረው ግለሰብ " የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በአፍሪካ ቀንድ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት አላዋቂ ሳሚ ዓይነት ጽሑፍ ተጠቃሽ ነው፡ ፡ የግለሰቡ ጽሑፍ በሰነዱ አማካኝነት በተጨባጭ እየተመዘገቡ ያሉትን ሃቆች የማያውቅ ሲሆን፤ በዋነኛነት ከ9 ዓመታት በኋላ በባነነ አዕምሮ ሰነዱን በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው፡፡

የፀሐፊው ትንተና ጋዜጣቸው ላይ እንደሚጽፍ ማንኛውም የማጥላላት ፖለቲካ ተከታይ እንደሚያደርገው በዕውቀት ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በሰሚ ሰሚ አሊያም ሁሉም "የፍትህ ፀሐፊዎች ነን" የሚሉ ወገኖች እንደሚከውኑት የፈረንጅ ስም ድረታና "ጥናት ያደረጉ ምሁራን"ወዘተ. ከሚል መነሻ የሚመነጭ ነው - ጭፍን ጥላቻ የጋረደው እንጂ፡፡ ምንም እንኳን አንድ ፀሐፊ የሚጽፈውን ርዕሰ ጉዳይ ከማንሳቱ በፊት ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ መያዝ እንዳለበት "አዘጋጅ" ነኝ ለሚል ግለሰብ መንገሩ ሃፍረትን የሚያጭር ቢሆንም፤ አቶ ሙሉነህ ያለ ሃፍረት ለመተቸት የሞከሩትንና ከሰነዱ ላይ ቀነጫጭበው በመውሰድ "ዶ ክመንቱ፣ እንዲህ ይላል፣ ግን እንዲህ ነው" በማለት የራሳቸውን ጨለምተኛ እሳቤ የዶሉበትን ሃሳቦች በተራ በተራ ለመመልከት እሞክራለሁ፡፡

የግለሰቡ ግራ የተጋባና በ”ዓይኔን ግንባር” ያድርገው ምልከታ “የደርግ ስርዓት ስለወደቀ፣ ኢህአዴግ ፖሊሲውን ማውጣት የግድ ብሎታል” የሚል አንድምታ ያለው ጽሑፍ ያው እንደተለመደው የፍትህ የፖለቲካ ቀመር “በዘርፉ ብዙ ጥናት ያደረጉ ምሁራን” (እነማን እንደሆኑ ባይታወቅም) በሚል ጥራዝ ነጠቅ የቃላት ጨዋታ እንጂ፤ እዚህ ግባ የሚባል ሃቅን የያዘ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ የደርግን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የቀየረው አምባገነኑን ሥርዓት ስለወደቀ ብቻ ሳይሆን፤ ፖሊሲው የሀገራችንን መሠረታዊ ችግር ከመቅረፍ አኳያ አንዳችም ፋይዳ ስላልነበረውና ሊኖረውም ስለማይችል ነው፡፡ ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ ጉዳዩን በውል እንዲነገዘቡት፤ እውነታውን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ፖሊሲ ሲቀረጽ የሀገሪቱን አንገብጋቢና ተጨባጭ ሁኔታን መነሻ ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ደርግ እንደወደቀ የነበረው ፈታኝ ሁኔታ የኢኮኖሚ ድቀት እንዲሁም የሠላም እና የዴሞክራሲ እጦት ነበር፡፡ በወቅቱ አምባገነኑን ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳይመለስ ግብዓተ መሬቱን የፈጸሙት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የነበረባቸው ችግር እንደ ሀገር ለመቆም ለህልውናቸው ወሳኝ የሆኑትን ውስጣዊ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲውም ይህንን መሰረታዊ እውነት ባገናዘበ መልኩ ድህነትን የሚያስወግድ፣ የኢኮኖሚ ልማትን፣ ብልጽግናን ፣ ዴሞክራሲንና ሠላምን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲነደፍ መደረጉ የትናንት ትውስታችን ነው፡፡

ምናልባት ፀሐፊው ‘ኢህአዴግ የደርግን ርዕዮት ሊከተል አስቦ ነበር’ የሚል አንድምታ ያለው መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልገው ከሆነ፤ አባባሉ ውኃ የማይቋጥር የጥንቆላ ትንቢት ከመሆኑም በላይ ፣ በጋረዳቸው የጥላቻ ሴራ ትንተና እንደ ጓደኞቻቸው የፍትህ አምደኞች የማይገናኙ ሁለት ነገሮችን በግድ ቀጥለው ለመስፋት የሞከሩ ያስመስልባቸዋል፡፡ እስቲ ሁለት ምክንያቶችን በአስረጂነት ልጥቀስ፡፡ የየሥርዓቶቹን ባህሪ እና የፖሊሲያቸውን የገዘፈ ልዩነት፡፡

ከባህሪ አኳያ የደርግን አምባገነናዊነትና ዘግናኝ ጭፍጨፋዎችን ማውሳት የውድ አንባቢዬን ጊዜ መሻማት ስለሚሆንብኝ አልፈዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ላይ ያሻቸውን እየጻፉና እያስጻፉ ብሎም ባሰኛቸው የፖለቲካ ርዕዮት እየተደራጁ ሁሉንም ህገ - መንግስታዊ መብቶች እንደፈለጉት እየተጠቀሙ ‘የፕሬስ ነጻነት የለም’ ለሚሉት የፍትህ ጋዜጣ የወረቀት ላይ አርበኞች ካልሆነ በስተቀር፤ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃቁ ፍንትው ብሎ የሚታይ በመሆኑ ነው፡፡

ሁኔታውን ከፖሊሲ ልዩነት አኳያ ስንመለከተው፤ ደርግ ሲከተለው የነበረው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከሥርዓቱ አምባገነናዊ ፖሊሲ በመነጨ ሁሉንም ጎረቤት ሀገሮች “በይወሩኛል” ጥርጣሬ ዓይን የሚመለከትና በጠብ የፈላለግ ስሜት የታጀለ ነበር፡፡ በውስጥ ያለውን ችግር ከመመልከት ይልቅ ጣቱን ወደ ውጭ በመቀሰር የሚታወቀው ይህ ፖሊሲ፤ ሀገሪቱን ለከፋ የኢኮኖሚ ድቀት ያዳረገ፣ ወደሚያበራ የእርስ በርስ ጦርነት የከተተ መሆኑ አሌ አይባልም፡፡ አናም ሀገሪቱ ከሰላም ዕጦት የነበረባትን ጥቅም በማስቀረቱም ባሻገር፤ ለአስከፊ ማህበራዊ ቀውስና ድህነት ዳርጓታል፡፡

ዕውቀት አጠሩ “ ፀሐፊ ተብዬ” እንዳሉት ሳይሆን በወቅቱ ኢሕአዴግ የደርግ ፖሊሲን የመከተል አንዳችም ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ቻርተሩን ሲነድፍ፤ የዜጎችን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠት በዘለለ፣ ለአፍሪካ ቀንድና ለአካባቢው ዘላቂ ሰላም መስፈን የሚያስችሉ አካሄዶችን በመከተሉ ነው፡፡ ይህም በሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት ያስቻለ ከመሆኑም ባሻገር ለመጀመሪያ ጊዜ በቀጣናው ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የተወሰደ ርምጃ ነው፡፡ ተግባሩም ለምስራቅ አፍሪካ ሰላም ወዳድ ህዝቦች መልካምና ጠንካራ የዲፕሎማሲያዊ ምዕራፍ የከፈተ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የሽግግር መንግሥቱን ቻርተር ተመርኩዞ የተዘጋጀውና በአሁኑ ወቀት ብሔራዊ ጥቅማችንን በማስጠበቅ ላይ ብሎም ሀገራዊ ህልውናችንን እያረጋገጠ የሚገኘው የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ፤ የውስጥ ችግሮቻችንን በመቅረፍ ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በጋራ ጥቅም እና ሰላም ላይ እንዲመሰረት ያደረገ ነው፡፡ ታዲያ ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ "በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን…" (ምናልባትም ትክክል ከሆነ ማለቴ ነው) እያሉ ሃቅን ያላገናዘበ የጥላቻ ዲስኩርን እንግቦ አራምባና ቆቦ መጻፍ ግምት ላይ የሚጥል እንጂ ረብ ያለው ጥቅም የሚያስገኝ አይመስለኝም፡፡

የዚህ ጹሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ በፖሊሲው ላይ የኢትዮጵያ መንግስት ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የሚከተለው መንገድ በግልጽ ተብራርቷል፡፡ ከቀጣናው ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት በመከባበር ላይ የተመሰረተ እንዲሁም ሰጥቶ በመቀበል መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ፀሐፊው ግን "ሰነዱ የሀገራቱን ተፅዕኖ እጅግ አሳንሶና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊም ይሁን ፖለቲካዊ የዕድገት ጋሬጣዎች ላይ አንዳችም አሻራ እንደሌላቸው አስቀምጧል" በማለት የፖሊሲውን መንፈስ በማያመላክት ሁኔታ የራሳቸውን ድምዳሜ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡

ይሁንና የግለሰቡ ድምዳሜ ፖሊሲው ከስሜት በራቀና በስከነ አዕምሮ ሀገሮቹ ከልማትና ከዴሞክራሲ አኳያ ለሀገራችን ያላቸውን በጎም ይሁን አሉታዊ ተፅዕኖ አኳያ ፋይዳቸውን በግልፅ የለየ መሆኑን በቅጡ ያወቁት እንኳን አይመስልም፡፡ ፀሐፊው ሰነዱን በቅንጫቢ መልክ ባይመለከቱት ኖሮ እውነታውን በውስጡ ባገኙት ነበር፡፡ ምንም እንኳን የሌለ አቅምን አለ ብሎ ለመግለጽ የማይቻል ቢሆንም፤ አንድ ሀገር የምትቀርጸው ፖሊሲ ጎረቤቶቿን አሳንሳ በመመልከት ላይ የተመሰረተ ይሆናል ማለት የዋህነት ነው፡፡

ሆኖም የቀጣናው ሀገራት ያላቸውን የካፒታልና የፋይናንስ እጥረት በማሳየት፤ ከኢኮኖሚ ልማት አኳያ በሀገራችን ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን መስተጋብር ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ምናልባት ፀሐፊው ሰነዱን በአግባቡ ካልተመለከቱት "…ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለን ተገንዝበን ከእነዚህ ሀገሮች ጋር የሚያገናኘንን ትክክለኛ ፖሊሲ መቀየስ ይገባናል…" በማለት ፖሊሲው ከቀንዱ ሀገራት ጋር የሚኖረን እጅግ የተቆራኘ መሆኑን በይፋ የገለጸውን እውነታ በተረዱት ነበር፡፡

ጻሩ ግን ከፖሊሲው ሰነድ ውስጥ ጥቂት ሰበዞችን መዝዞ "ዶክመንቱ እንዲህ ይላል፣ አሁን ግን እንዲህ እየሆነ ነው" በማለት ጭብጡን ሳይዙ በድፍረት በጉዳዩ ላይ ለመጻፍ መነሳት፤ የተቃውሞ ጎራ ሁሉንም ነገር የማጥላላት አባዜው የት ድረስ እንደሚዘረጋ የሚያሳየን ነው፡፡ አስገራሚው የግለሰቡ "ትንተና" በዚህ ብቻ የተገታ አይደለም- "ከተፈጥሮ ሀብት አኳያ ሲታይ በውኃ አጠቃቀም ረገድ ዋነኛውን

የሰነዱን መንፈስ ሆን ብለው ዘለውት፤ “ፖሊሲው የቀንዱ ሀገራት የውኃ ሀብት አጠቃቀማቸው ውስን በመሆኑ እኛ የውኃ ሀብታችንን ብንጠቀም ከባድ እንቅፋት የሚሆኑ አይደሉም” ሲል መግለፁን በመተቸት፤ ሰነዱ “ነገን የተመለከተ አይለደም” የሚል አንድምታ ያለው ትንተና አቅርበዋል፡፡

ውድ አንባቢዎቼ! እንኳን አንድ ሀገር የምታዘጋጀው ፖሊሲ ቀርቶ በግለሰብ ደረጃ የሚነደፍ ዕቅድ እንኳን “ነገን” በአግባቡ አንጥሮ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ፖሊሲው በይፋ ለህዝብ የተሰራጨው በ1995 ዓ.ም በመሆኑ 10 ዓመታትን ሊያቆጥር የቀሩት በጣት የሚቆጠሩ ወራት ብቻ ናቸው፡፡ እናም “ነገ” ማለት ቢያንስ ከፖሊሲው ይፋ መሆን በኋላ ያሉት ዓመታት ናቸው፡፡ ጸሐፊው ከየት እንዳመጡት ባይታወቅም እርሳቸው “የጎረቤት ሀገራት በተለይም ሱዳንና ኬንያ በአሁኑ ወቅት ለውኃ አጠቃቀማቸውን ዙሪያ ትልቅ ስጋት እና እንቅፋት ናቸው” በማለት ያቀረቡት የደርግ ሥርዓት ዓይነት ሁሉንም ነገር በጥርጣሬ እና በስጋት የመመልከት አባዜ “ትንተና” መሬት ላይ ያለውን ሃቅ የሚያንጸባርቅ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከውኃ አጠቃቀም መርህ አኳያ ሱዳንና ኬንያ የሀገራችን ልማት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉበት ነባራዊ ሁኔታ የሌለ መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ እርግጥ በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ዘላቂ ወዳጅም ይሁን ዘላቂ ጠላት ሊኖር አይችልም፡፡ ዓለማችን በፈጣን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የእሽክርክሪት ለውጥ ውስጥ የምትገኝ በመሆኗ፤ ቋሚ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን ማለም የማይታሰብ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና መንግስት ባለፉት 8 እና 9 ዓመታት ውስጥ ያከናወናቸውና ተሰሚነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጎለብት ያደረገው የዲፕሎማሲ ድል፤ ጎሬቤቶቻችን ከልማታችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ምንም እንኳን ሱዳን ቀደም ባሉት ጊዜያት የዓባይ ውኃን በተመለከተ ያላት አቋም ከግብጽ ጋር ያበር የነበረ ቢሆንም፤ በአሁኑ ወቅት ግን ኢትዮጵያ የምትገነባው ታላቁ የህዳሴ ግድብ በደለል እንዳትዋጥ እንዲሁም ከሚመነጨው ኃይል ተጠቃሚ እንደምትሆን በማወቋ ግድቡ እንደሚጠቅማት በማያሻማ ሁኔታ ተገንዝባለች፡፡ ለዚህም ነው በኢትዮጵያ የሀገሪቱ አምባሳደር በየጊዜው ግድቡ ከሀገራችን አልፎ ለሱዳን ህዝብና መንግስት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ሳያሰልሱ ሲናገሩ የምናደምጣቸው፡፡

ከዚህ ውጭ ግለሰቡ የደርግን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ከተቀበረበት ከ21 ዓመት በኋላ አዋራውን አራግፈው “መስጋት አለብን” የሚሉ ከሆነ፤ የስጋት “ፖሊሲያቸውን” በተለመደው ጋዜጣቸው ላይ ገቢራዊ ቢያደርጉት የሚሻል ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም እንደ እኔ የአንድ ሀገር ህዝብና መንግስት “በእናንተ ልማት እኛም ተጠቃሚ ነን” ሲል ልንጠራጠራቸውና በስጋት ቆፈን ውስጥ ሆነን ልናርቃቸው የምንችልበት ምንም ዓይነት ተጨባጭ ምክንያት ሊኖረን ስለማይችል ነው፡፡

ኬንያም ብትሆን የልማታችን አጋር እንጂ፤ እንቅፋት አይደለችም፡፡ ፀሐፊው በስሚ ሰሚ “የኬንያ መንግስት በግልገል ጊቤ - ሦስት ፕሮጀክት ምክንያት የቀድሞ መልኩን እየቀየረ መጥቷል” በማለት ያሰፈሩት ሃሳብ በግልጽ የሚታወቅ መንግስታዊ ምንጭን ዋቢ ያደረገ አባባል አይመስለኝም፡፡ ለእኔ ካልተጨበጠ ተነስቶ በምናባዊ ህልም አንድ ሀገር “አቋሙ ተቀይሯል” ብሎ መጻፍ ምን ዓይነት

“ጋዜጠኝነት” እንደሆነ ሊገባኝ ባይችልም፤ የኢትዮጵያ መንግስት በኦሞ ወንዝ ላይ እየገነባ ስላለው የግልገል ጊቤ - ሦስት የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክትን አስመልክቶ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡

ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ በመገንባት ላይ የሚገኘውና ስራው ከግማሽ በላይ እየተጠናቀቀ ያለው የግልገል ጊቤ - ሦስት ፕሮጀክት በኢትዮጵያና በኬንያ መንግስታት የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ግድብ በቱርካናም ሃይቅ ይሁን በአካባቢው በሚኖሩት ጎሳዎች ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ተፅዕኖ የለም፡፡ ይልቁንም በግድቡ ዙሪያ ለሚገኙ ህዝቦችና ለሃይቁ የጎላ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም በላይ፤ የሁለቱን ሀገራት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክረው መሆኑን ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡

እርግጥ ምንጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያን ዕድገት ማየት የማይሹ እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎችን የመሳሰሉ ጽንፈኛ ኒዮ - ሊበራል ኃይሎች፤ የሀገራችንን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ጉዞ ለማደናቀፍ እግር በእግር እየተከታተሉ በመግለጫ ጋጋታ እንደ ሌሎቹ የመንግስት ልማታዊ ተግባራት ሁሉ ፕሮጀክቱን ለማቋረጥ ለማጣጣል ሞክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ፤ አልተሳካላቸውም፣ መቼም ሊሳካላቸውም አይችልም፡፡

ግራ የተጋባው የፀሐፊው የፖሊሲ “ትንተና” ምናልባትም የእነዚህን ኃይሎች እምነት ለማስተጋባት ታስቦ ከሆነ፤ የአንድ ሀገር የውጭ ግንኙነት አካሄድ የራሳቸውን የፖለቲካ ፍላጎት ለማራመድ በሚሹ አክራሪዎች የሚቀየር አለመሆኑ መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ እናም የኢትዮ - ኬንያ የጉርብትና እና በጋራ አብሮ የማደግ ራዕይ በመንገድ፣ በንግድ ብሎም በጊቤ - ሦስት ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚት እንደሚረጋገጥ ጸሐፊው ቢገነዘቡት በጄ ነው፡፡

የፍትህ ጋዜጣው “አዘጋጅ” በፖሊሲው ሰነድ ላይ የተቀመጠውን የኤርትራንና የሶማሊያን ጉዳይንም “የሀገራችንን መሪዎች ወጥ አቋም አያንጸባርቅም፤ ለጊዜው ብቻ መፍትሄ የሚሰጥ ነው” በሚል ሽውራራ እይታ ተመልክተው ሊተነትኑት መሞከራቸው ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ነው፡፡ ከኤርትራ አኳያ በዋነኛነት ያስቀመጡት ነጥብ “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የኢሳያስ መንግስትን ከስልጣን ለማባረር የተቻለንን እናደርጋለን እያሉ፤ ፖሊሲው ግን ይህንን ለውጥ የማምጣት የእኛ ስራ አይደለም ይላል - እናም ይቃረናል” የሚል ነው፡፡ እርግጥም ይህ አባባል ግለሰቡ ስለ ፖለቲካ ምንም ዓይነት ዕውቀት የሌላቸው እንዲሁም ማንኛውንም ጉዳይ በድፍረት በራሳቸው የጥላቻ መዝገበ - ቃላት የሚመነዝሩ መሆናቸውን የሚያሳብቅ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ‘ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ለማለት ፈልገው ነው?’ ብሎ እንደ ጋዜጠኛ በሰከነ ሁኔታ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማ የመንግስታቸውን አቋም በገለጹበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የአስመራው መንግስት ኢትዮጵያን የማተራመስ ስትራቴጂውን እስካላቆመ ድረስ መንግስት ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚወስድና የሻዕቢያውን ቡድን ለመጣል ለሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ድጋፍ ይሰጣል

ብለዋል። ይህ ማለት 'እኛ ራሳችን ኤርትራ ውስጥ ገብተን የሀገሪቱን መንግስት እንገለብጣለን' የሚል አንድምታ እንዴት ሊኖረው እንደሚችል የሚያውቁት ፀሐፊው ብቻ ናቸው፡፡

በመሆኑም አባባላቸው በፖሊሲው ላይ ከተቀመጠውና "... በኤርትራ ውስጥ የፖለቲካ ለውጥ ማምጣት የእኛ ስራ አይደለም፡፡... በመሆኑም ከቁጥጥራችን ውጭ የሆነና በኤርትራ ህዝብ እጅ ያለ ጉዳይ ነው፡፡..." ከሚለው ዋነኛ መርህ ጋር የሚጋጭም ሆነ የሚቃረን አይደለም፡፡ የሀገራችን መሪዎች ወጥ አቋምና እምነት ያላቸው መሆናቸውን ቢያንስ ለጠቅላላ ዕውቀት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እርግጥ ነገሮችን በራሱ ተቃራኒ ዕይታ ለመተርጎም የሚከጅል ግለሰብ፣ ተግባሩ ሁሉ የተጣመመ ነገርን ሁሉ ሲያይ ሚስማር እንደሚመስለው አናጺ ዓይነት በመሆኑ የፀሐፊውን ማንነት ከዚህ አኳያ ለመመልከት አይከብድም፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ፖሊሲ ዝርዝር አፈጻጸሞችን አያካትትም – ሁኔታዎች ተለዋዋጭ ናቸውና፡፡ ይሁንና ወሳኝ የሚባሉ አንኳር ጉዳዮችን ይዘረዝራል፡፡ ከዚህ በመነሳት የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ከሶማሊያም ይሁን ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የገለጸው ይህንኑ መርህ ተከትሎ ነው፡፡ ዳሩ ግን "እንዲህ ሊሆን ስለሚችል፣ እንዲህ የሚል ምላሽ ፖሊሲው ውስጥ ስለሌለ አገላለጹ ውስን ነው" ማለት ምናልባትም የፀሐፊው የፖለቲካ "ህሁን" ቀጣሪነት የሚያሳብቅ ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ፀሐፊው "የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው የሶማሊያን መሰረታዊ ችግር ለመዳሰስ ያደረገው ጥረት ውስን ነው" በማለት ያሰፈሩት ሃሳብ ውኃ የማይቋጥር አተያይ ለመሆኑ ራሱን ፖሊሲውን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሰነዱ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው፣ ሀገራችን በሶማሊያ ላይ የምትከተለው ፖሊሲ በዋናነት የሀገሪቱን ሠላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በሚያስችል መልኩ ገቢራዊ የሚሆን ነው፡፡ ይህም በዚያች ሀገር ያለው አለመረጋጋት ቢቀጥል ወደ ሀገራችን ወይም ወደ አካባቢው አሊያም በሶማሊያ ህዝብ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ታስቦ የተዘጋጀ መርህ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

የአንድ ሀገር ፖሊሲ በሌላኛው ሀገር ውስጥ ለዕድገትና ለመረጋጋት እጅግ ቁልፍ የሚባሉትን ሠላምና ዴሞክራሲን እንዲሰፍን እንጥራለን ከማለት ውጭ፣ እያንዳንዱን አፈጻጸም ደረጃ በደረጃ ሊዘረዝር አይችልም፡፡ ከዚህ አኳያ በሶማሊያና በአካባቢው ሀገራት ላይ ኢትዮጵያ የምትከተለውን ፖሊሲ በተገቢው ሁኔታ መግለጹን ግለሰቡ መልሰው በንጹህ አስተሳሰብና ከጥላቻ በጸዳ አዕምሮ ደግመው ሊያነቡት የሚገባ ይመስለኛል፡፡

ጸሐፊው በሰነዱ ላይ "የታላቋ ሶማሊያ መፈክር እንደገና ቢነሳም፣ ባይነሳም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነትና በአንድነት መኖረን የሚመርጡበትን ሁኔታ ፈጥረናል" ተብሎ የተገለጸው አባባልም ትክክለኛ መሆኑን ሊስቱት አይገባም፡፡ ምንም እንኳን የህዝቦችን እኩልነትና አንድነት እንደማያምን ማንኛውም ወገን ግለሰቡ ያሻቸውን ቢሉም፣ ላለፉት 21 ዓመታት ሶማሊያውያን ከኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻቸው ጋር በእኩልነትና በአንድነት እንዴት እንደሚኖሩ፣ በሶማሌ ክልል የሚገኙ የስደተኞች ጣቢያን መመልከት ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡

ከዚህ ውጭ መንግስት በፖሊሲው ላይ በግልጽ በደነገገው መሰረት የሶማሊያን ሠላምና ዴሞክራሲን በማምጣት ሀገራችንንና ከባቢውን ከስጋት ለመታደግ የሚደረግን ተግባር በመጥቀስ፤ የሶማሊያ ህዝብ ወንድሙ ከሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እኩልነትና አንድነት እንደሌለው አድርጎ መተንተን ከፀረ - ህዝብነት በስተቀር በሌላ የሚያስፈርጅ አይመስለኝም፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፤ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን በምርኩዝነት ይዞ ላለፉት ዓመታት በሰከነና በሳል አመራር እየታገዘ ዛሬ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያ መንግስት የአንጸባራቂ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች ባለቤት ነው፡፡ እነዚህ ድሎች ሀገራችንን በብሔራዊ ጥቅም ያረጋገጡ፣ እኩልነትንና የጋራ ተጠቃሚነትን ያጎለበቱና ቀጣናዊ ትብብርን የፈጠሩ ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህን ትሩፋቶች የጥላቻ አጀንዳን ባነገቡ ጥቂት ወገኖች አላዋቂ ልፈፋ የሚሻሩ አይሉም– ፖሊሲው እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ሆነ ነገ ቀጣይ እመርታዎችን እንዲያስመዘግብ ተደርጎ ታስቦበትና ታቅዶ የተዘጋጀ ነውና፡፡